የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
Ethiopian Agricultural Authority

# ዜና መፅሔት

በሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ በየ2 ወሩ የሚወጣ የውስጥ ጋዜጣ

ቅጽ 1 ቁጥር 69 ግንቦት 2017ዓ.ም

## ርዕይ

በዓለምአቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም ሆኖ ማየት፤

## ተልዕኮ


የግብርና ቴክኖሎጂን፣ አገልግሎቶችን፤ ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ ደህንነት፣ ፍቱንነት፣ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤ መልካም ስም ያለውና፣ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓት በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኤኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት

## እሴቶች

- ታማኝነት
- ሚስጥር ጠባቂነት
- ቁርጠኝነት
- የህግ የበላይነት
- ተጠያቂነት
- ለደንበኛና ተገልጋይ ትኩረት
- አለማዳላት
- አጋርነት
- ግልጽነት።
- ምላሽ ሰጪነት

አድራሻ፡- ፖ.ሳ.ቁ 31303
ስልክ ቁጥር ፡- 0115534520
የውስጥ መስመር፡- 227/234
ዌብሳይት:- http:www.eaa.gov.et
ፌስቡክ:- Ethiopian Agricultural Authority
ቴሌግራም:-eaapr_1234

## የጥራት ምርመራ ማዕከሉ በቀጣይ ለሚሰራቸው ስራዎች በተለይም ዕውቅና የተገኘባቸው የላቦራቶሪ ምርመራ እና የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ ሥራዎችን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገለፀ።



የእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራት ምርመራ ማዕከል ሰኔ 2006 ዓ/ም የተቋቋመ ሲሆን ማዕከሉ ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ነው። ዓላማውም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ምርቶችን ጥራት፣ ተስማሚነት በላበራቶሪ ፍተሻ ሥራ በማረጋገጥ የእንስሳት እና የህብረተሰብ ጤና አገልግሎትን ማሻሻል ነው። በመሆኑም በመጀመሪያዎቹ ጥቂት አመታት በርካታ ሥራዎችን በመፈጸም ተቋሙን በሰው ኃይል እና አስፈላጊ የላበራቶሪ ግብአቶች እንዲሟላ በማድረግ በ2009 ዓ/ም መጨረሻ አከባቢ በተመረጡ የእንስሳት መድኃኒት ናሙናዎች ላይ የላበራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት መስጠት ጀመረ። በዚህም መሰረት ማዕከሉ ደረጃውን

የጠበቀ የእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራትና ደኅንነት እንዲኖር የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት በመስጠት የእንስሳት ጤና፣ ምርታማነትና የገበያ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ተመራጭ የልሕቀት ማዕከልና ዓለማቀፍ ተቀባይነት ያለው የጥራት ምርመራ ላብራቶሪ ሆኖ ለመስራት ይገኛል።

የምርመራ ማዕከሉ ከሚሰራቸው በርካታ ስራዎች መካከል፡- የላበራቶሪ ጥራት ምርመራ ሥራዎች ተግባራዊ በማድረግ ለውሳኔ የሚረዳ ተአማኒነት እና ተቀባይነት ያለው የላበራቶሪ ምርመራ ውጤት መረጃ ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማቅረብ፣ የእንስሳት መድኃኒት ምርት

ወደ ገጽ 2 ዞራል!

**ከገጽ 1 የዞረ..**

ጥራት፣ ፈዋሽነት እና ደህንነት ቁጥጥር የላበራቶሪ ምርመራ አገልግሎት በመስጠት የአገራችን የእንስሳት በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆን ድጋፍ ማድረግ፣ የእንስሳት መኖ ምርት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር የላበራቶሪ ምርመራ አገልግሎት በመስጠት ለአገራችን የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ዕድገት አስተዋጽኦ ማበርከት፣ የእንስሳት ውጤቶች የኬሚካል ቅሪትና ደቃቅ ተዋስያን ብክለት የቅኝትና ክትትል ሥራዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ የህብረተሰብ የጤና ስጋት ተጋላጭነት መከላከል እና የእንስሳት ተወጽኦዎች የአገር ውስጥና አለም አቀፍ የገበያ ተወዳዳሪነት ማሳደግ፣ ስጋትን መሰረት ያደረገ የእንስሳት መድኃኒት ጥራትና ደህንነት የድህረ ገበያ የዳሰሳ ጥናትና የቅኝት ተግባራትን ማከናወን፣ ጠንካራ የላበራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ የላበራቶሪ አገለግሎት አሰጣጥ ደረጃ የበለጠ ማሳደግ እና ተቋሙ ባገኘው የአለም አቀፍ ተቀባይነትና እውቅና መሰረት የአሰራር ስርዓቱን በተሻለ ተወዳዳሪ ማድረግ፣ የጥራት ምርመራ ላበራቶሪ መሰረተ ልማት ማስፋፋትና የአገልግሎት አቅም እና ተደራሽነት ማሳደግ፣ የላበራቶሪ ግብዓት አቅርቦት፣ አጠቃቀም እና ማኔጅመንት ስርዓት ማሳደግ ሲሆን በተጨማሪም Laboratory testing services rendered by the Center ማዕከሉ የሚሰጣቸው የላበራቶሪ ምርመራ አገልግሎቶች Veterinary drugs quality, efficacy & safety testing የእንስሳት መድኃኒት ጥራት፣ፈወሽነትና ደህንነት ምርመራ፣ Vaccines quality, safety & potency testing የክትባት መድኃኒት ጥራት፣ብቃትና ደህንነት ምርመራ፣ Nutritional content/ proximate analysis (milk, feed) የምግብ ይዘት/ጥንቅር ምርመራ (ወተት፣መኖ)፣ Mycotoxins analysis (milk, feed) የማይኮቶክሲን ምርመራ (ወተት፣መኖ)፣ Toxic mineral analysis (meat, milk, feed, honey) የመርዛማ ሚኔራል ምርመራ (ሥጋ፣ወተተ፣ማር፣መኖ )፣ Veterinary drug residues analysis (meat, milk, honey) የእን/መድኃኒት ቅሪት ምርመራ (ሥጋ፣ወተት፣ማር)፣ Pesticide residue analysis (honey, milk, meat) የፀረ-ተባይ ቅሪት ምርመራ (ማር፣ሥጋ፣ወተት)፣Miro/organism enumeration testing (meat, milk, feed) የማይክሮኦርጋኒዚም መጠን ቆጠራ ምርመራ፣ Food/feed borne pathogen bacteria identification የምግብ/መኖ ወለድ ጎጂ ባክቴሪያ ልየታ/ምርመራ፣ Antimicrobial Resistance (AMR/AST) testing የጸረ ተዋሲያን መድኃኒት በጀርሞች መላመድ ምርመራ ናቸው፡፡

የእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራት ምርመራ ማዕከሉ በአለም አቀፍ ደረጃ በ13 የጥራት ምርመራ አይነቶች ላይ ዕውቅና አግኝቷል፡፡

1 Albendazole identification by UV-Vis spectroscopy አልቤንዳዞል አደንተፊኬሽን በዩቪ-ቪስብል ስፔክተሮስኮፒ

2) Albendazole weight variation by acceptance limit አልቤንዳዞል ዌይት ቫሬሽን ባይአክሰፕታንስ ሊሚት

3) Albendazole, Oxytetracycline & Ivermectin identification by retention time by chromatography አልቤንዳዞል ኦክስቴትራሳይክሊንና አይቨርሜክቲን አደንተፊኬሽን በክሮማቶግራፊ

4) Albendazole, Oxytetracycline & Ivermectin Assay [Active Pharmaceutical Ingredients (API) determination] by Chromatography አልቤንዳዞል ኦክስቴትራሳይክሊንና አይቨርሜክቲን የፈዋሽነት ንጥረ ነገር ይዘት ምርመራ በክሮማቶግራፊ

5) Injectables and oral drugs pH measurement በመርፌናበአፍ የሚሰጡ መድኃኒቶች ፒኤች ሜዠርመንት

PAGE 3

**ከገፅ 2 የዞረ**

6) Non-sterile VMPs microbial limit test የእንስሳት መድኃኒቶች የባካይ ተወሲያን መጠን ምርመራ

7) Sterile VMPs sterility test by direct inoculation የእንስሳት መድኃኒቶች ስቴሪሊቲ ምርመራ

8) Animal feed Total aflatoxin testing by chromatography የእንስሳት መኖ ቶታል አፍላቶክሲ ምርመራ

9) Raw milk aflatoxin (M1) testing by chromatography የጥሬ ወተት አፍላቶክሲን (ኤም ዋን) ምርመራ

10) Identification of Salmonella species in food/ feed stuffs ከምግብና መኖ የሰልሞኔላ ስፒሽስ ልየታ ምርመራ

11) Identification of Staph.aureus in food/feed stuffs ከምግብና መኖ የስታፍሎኮከስ አውረየስ ልየታ ምርመራ

12) Identification of Escherichia coli in food & feed stuffs ከምግብና መኖ የኢኮላይ ልየታ ምርመራ

13) Aerobic Plate Count (APC) in food & feed stuffs ከምግብና መኖ የኤሮብክ ፕሌት ካወንት ምርመራ ናቸው።

የጥራት ምርመራ ማዕከሉ በቀጣይ ለሚሰራቸው ስራዎች ላይ በተለይም ዕውቅና የተገኘባቸው የላቦራቶሪ ምርመራ እና የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል፣ የላቦራቶሪ ኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ፣ የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎቶችን በማስፋት የምግብ ማይክሮባዮሎጂና የኬሚካል፣ ቅሪት ምርመራ አክሪድቴሽን ወሰን ማሳደግ፣ የጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ መሰረተ ልማት ግንባታ እና የአገልግሎት ሽፋን ተደራሽነት ማሳደግ፣ የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦት እና ማኔጅመት ስርዓት ማሻሻል፣ የላቦራቶሪ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል፣ የእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ቁጥጥር እና ቅኝት ሥራዎችን ማሳደግ ናቸው።





**ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድሀኒት አቅርቦትን ለማሳደግ የባለድርሻ አካላት ሚና ወሳኝ መሆኑ ተገለፀ ።**

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድሀኒት አቅርቦትን ለማሳደግ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ የእንስሳት ሀኪሞች ማሕበር፣ ከብሩክ ኢትዮጵያ እና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ውይይት አካሄደ።

ወደ ገፅ 4 ዞሯል

**ከገፅ 3 የቀጠለ**

በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእንስሳት ዘርፍ ሪጉላቶሪ ም/ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ሀሚድ ጀማል በመክፈቻ ንግግራቸው የስልጠናው ዋና ዓላማ ባለፉት አራት አመታት በአገር አቀፋ ደርጃ የተዘጋጁትን መሰረታዊ የእንስሳት መድሀኒት ዝርዝር ላይ ለክልል ባለሙያዎችና ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤን በመፍጠር ወደ ተግባር ለመግባት እና ጥራቱ፣ ደሕንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድሀኒት አቅርቦትና የእንስሳት መድሀኒት አማራጮችን ለማሳደግ ነው ብለዋል። ዶ/ር አያይዘውም የእንስሳት መድሀኒት አቅርቦቱ የተሳለጠና ውጤታማ እንዲሆን የባለድርሻ አካላት ሚና ወሳኝ መሆኑን ገልፀዋል።በባለስልጣኑ የእንስሳት መድሀኒት ሪጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር ሰለሞን ከበደ የእንስሳት መድሀኒት አቅርቦት የተሻለ እንዲሆን ባለስልጣኑ እየሰራቸው ያሉ ስራዎችን በተመለከተ የመድሀኒት ዝርዝሩን በማዘጋጀትና በማስተባበር ፣መሰረታዊ የሚባሉ መድሀኒቶችን ቀላልና ፈጣን የአመዘጋገብ ስርዓት በመፍጠርና ለክልሎች ግንዛቤን መፍጠር አስመልክቶ በተሰሩ ስራዎች ላይ ሰፊ ገለፃ አድርገዋል።በባለስልጣኑ የእንስሳት መድሀኒት ምዝገባና ፈቃድ ከፍተኛ ባለሙያ የሆኑት ዶ/ር ሀይሉ ዘሩ አጠቃላይ በእንስሳት መድሀኒት አቅርቦት ላይ ያሉ ተግዳሮቶችና የባለድርሻ አካላት ሚና በሚሉ ሀሳቦች ላይ ግልፅ ውይይት አካሂደዋል።

የኢትዮጵያ እንስሳት ሀኪሞች ማህበር ስራ አስፈፃሚ ፕሮፌሰር እንድርያስ ዘውዱ እና ሌሎች ሙሕራን እንደ እንስሳት ጤና ባለሙያ የእንስሳት ጤና አገልግሎቱን ለማጠናከርና መሰረታዊ የእንስሳት መድሀኒት አቅርቦቱን ለማሻሻል ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ አሳስበዋል።

**ማንኛውም የግብርና መሰሪያዎች ጥራታቸው ሳይረጋገጥ ወደ ሀገር ገብተው አግልግሎት አይሰጡም -የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን**





የግብርና መካናይዜሽን አገልግሎት ግብርናን በቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ እና በማዘመን ፣ምርትና ምርታማነትን በመጨመር እንድሁም በምግብ ራስን ለመቻል ሚናው የጎላ ነው ፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የግብርና መሰሪያዎች አምራች፣ አስመጪ እና ላኪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር ረቂቅ መመሪያ እና የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር ረቂቅ መመሪያዎችን ባለድርሻ አካላት በተገኙበት አስገምግሟል።

**ወደ ገፅ 5 ዞሯል**

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ በመድረኩ ላይ የተገኙ ሲሆን ፤ የሀገራችንን የግብርና ምርቶች ምርታማነት ማሳደግ የሚቻለው ጥራት ያለውና የዘመነ የግብርና ቴክኖሎጂ እና የእርሻ መሳሪያ መጠቀም ሲቻል ነው ብለዋል።

ባለስልጣኑ ረቂቅ መመሪያዎቹን መሰረት በማድረግ የግብርና ማምረቻ መሳሪያዎችን ጥራትና ደህንነት እንድሁም አምራችና አገልግሎት ሰጭዎችን ብቃት በማረጋገጥ ለሀገራችን ግብርና እድገት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው ብለዋል።

ማንኛውም የግብርና መሳሪያዎች ፣የግብርና ግብዓቶች ፣ ምርቶች ባለስልጣኑ ጥራታቸውንና ብቃታቸውን ሳያረጋግጥ ወደ ሀገር ውስጥ እንደማይገቡና ወደ ውጭም እንደማይላኩ ዋና ዳይሬክተሩ ገልፀዋል።

በግብርና ሚኒስቴር የግብርና መካናይዜሽን አማካሪ የሆኑት አቶ ታምሩ ሀብቴ ወ/ማርያም በበኩላቸው ፤ የዚህ መመሪያ መዘጋጀት ሁሉም በግብርና መካናይዜሽን ስራ ላይ የሚሳተፉ አካላት በሙሉ አሰራሩን በትክክል አውቀው ለግብርና መካናይዜሽን መስፋፋት እና ለሀገራችን ግብርና መዘመን አስተዋጽኦ ማድረግ እንድችሉ እድል የሚሰጥ ነው ብለዋል።

አቶ ታምሩ አክለውም ለግብርና ስራ የሚውሉ በሀገር ውስጥ የተገጣጠሙና ከውጭ ሀገር ገብተው ልማት ላይ የዋሉ የግብርና መሳሪያዎች የሀገሪቱን የግብርና ፍላጎት የሚያሟሉ መሆናቸውን፣ የሀገሪቱን የአየር ንብረትና ስነ-ምህዳር ተስማሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይህ ረቂቅ መመሪያ ጠቃሚና ሚናው የጎላ መሆኑን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የግብርና ምርምር ፤ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ሬጉላቶሪ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ሰለሞን አመዴ፤ ጥራታቸውና አስተማማኝነታቸው የተረጋገጠ የግብርና ምርት ማምረቻ መሳሪዎች እና አምራች ተቋማት ለመፍጠር ባለስልጣኑ በሚያደረገው የቁጥጥር ስራ ረቂቅ መመሪያዎቹ አጋዥ ናቸው ብለዋል።

ዶ/ር ሰሎሞን አክለውም በውይይት በመድረኩ ላይ የተነሱ ረቂቅ መመሪያዎቹን የሚያጠናክሩ ጠቃሚ ግብዓቶች እንዲካተቱ ይደረጋል ብለዋል።

**የእፅዋት ምርት፣ ጥራትና የምግብ ደህንነትን ለማስጠበቅ በዘርፉ የሚገኙ ባለሙያዎችን ግንዛቤ ማሳደግ እንደሚገባ ተገለፀ።**








ወደ ገፅ 6 ዞሯል

ከ ገፅ 5 የዞረ

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእፅዋት ኳራንቲን ሪጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ የእፅዋት ምርት ጥራት፣ የምግብ ደህንነትና የተባይ ትንተና ስጋትን በተመለከተ አዲስ በዝውውር ለመጡ የዘርፉ ባለሙያዎች ግንዛቤን ፈጥሯል።

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የአገልግሎት አሰጣጡን በአጭር ጊዜ ውስጥ አሻሽሎ በመምጣት 66 የሚሆኑ አገልግሎቶችን በዲታላይዜሽን ሲስተም እየሰጠ ይገኛል ያሉት የባለስልጣኑ በእፅዋት ሪጉላቶሪ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ክቡር ዶ/ር ወንዳለ ሀብታሙ አያይዘውም 10 የሚሆኑ አገልግሎቶች ደግሞ በሞሰብ ተካተው እየተሰሩ መሆኑን ገልጸዋል።

ዶ/ር ጨምረውም ባለስልጣኑ የሪጉላቶሪ ስርዓቱ የተሳለጠና መልካም ስም ያለው ተቋም እንዲሆን ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ የእፅዋት የቁጥጥር ስራዎችና ኤክስፖርት ሰርተፋኬሽን ላይ የእፅዋት ምርቶች ፣ጥራት፣ የምግብ ደህንነትና የተባይ ስጋት ትንተና ስራዎችን በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች በአግባቡ ተረድተው በጥንቃቄና በአገልጋይነት መንፈስ በትኩረት መስራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

በባለስልጣኑ የእፅዋት ኳራንቲንና ሪጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ ወ/ሮ መቅደስ ነጋ አዲስ በስራ ክፋሉ በዝውውር ለመጡ ባለሙያዎች የእፅዋት ኳራንቲን ሬጉላቶሪ የሚሰራቸውን አጠቃላይ ስራዎች ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ እፅዋት፣ የእፅዋት ውጤት እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሶች ጤንነታቸውን፣ ጥራትና ደህንነታቸውን ጠብቀው አስፈላጊውን ምርመራና ፍተሻ በማድረግ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግና ወደ ውጪ በሚወጡ እፅዋት፣ የእፅዋት ውጤት እንዲሁም ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች ጤንነታቸውን፣ ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲሁም የተቀባይ አገር መስፈርት አሟልተው እንዲወጡ ለማድረግ ከዘርፉ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ሰፊ ግንዛቤን ፈጥረዋል።

በመጨረሻም ባለሙያዎች ስልጠናው ያላቸውን ግንዛቤ እንዳሳደገላቸውና ጥሩ የልምድ ልውውጥ እንዳገኙበት ተናግረዋል።

## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የህፃናት ማቆያ አስመረቀ።





PAGE 7




ሰኔ 6/2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የህፃናት ማቆያ ያስመረቀ ሲሆን በዕለቱ የተገኙት የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ የህፃናት ማቆያው ሴት ሰራተኞች ልጆቻቸውን በቅርበት እየተከታተሉ ስራቸውን እንዲሰሩ ምቹ ሆኔታ የሚፈጥር ሲሆን ከዚህ በተሻለ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በትኩረት እየተሰራበት መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በባለስልጣኑ የሴቶችና ማህበራዊ አካቶ ትግበራ ስራ አስፈፃሚ ወ/ሮ ትዕግስት ወንድማገኝ የህፃናት ማቆያው ተመርቆ ወደ ስራ መግባቱ ምቹ ስራንና አካባቢን ከመፍጠሩ ባለፈ በተለይም በልጆችና በስራው ላይ የሚፈጠረውን ጫና ይቀንሳል ብለዋል።

ወ/ሮ ትግስት አክለውም የህፃናት ማቆያው ለወደፊት የተሻለ ለማድረግ ተቋሙ በአንክሮ እየሰራበት መሆኑንም ገልፀዋል።

## ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሰራተኛውን ግንዛቤ ማሳደግ እንደሚገባ ተገለፀ።



የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ዙሪያ "ሙስናን ለመከላከል የዜግነት ግዴታየን እወጣለሁ"በሚል መሪ ሃሳብ ከሰኔ 13 /2017 ዓ.ም ጀምሮ ለሁለት ቀናት 3ኛውን ዙር ስልጠና ለሰራተኞች ሰጥቷል።

በስልጠናው ላይ ተግኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የጽ/ቤት ሃላፊ አቶ መሰሉ ዋጋው፤ ባለስልጣኑ አገልግሎቶቹን በሙሉ ዲጂታላይዝ በማድረግ አሰራሩን ማዘመኑን እና የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርምን ተግባራዊ በማድረግም ለተሞክሮ የሚሆን የተሻለ አፈፃፀም እንዳለው ገልፀዋል።

ተቋሙ ያቀደውን ግብ እንዲያሳካና የሪጉላቶሪ ስራው የተሳለጠ እንዲሆን ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አኳያ የሰራተኛው ሚና ወሳኝ ነው ብለዋል ።

ወደገፅ 8 ዞሯል

## ከገፅ 7 የዞረ

አቶ መሰሉ አክለውም የተቋሙ ሰራተኞች ሙስናንና ብልሹ አሰራርን በመፀየፍ እንደ ተቋምም ይሁን እንደ ሀገር በሚደረገው ዘመቻ ላይ የበኩላችንን ሚና ልንወጣ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

ከፌደራል ስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዶ/ር አወቀ አሸናፊ የሙስና ወንጀል ምንነት ፣የሙስና አይነቶች ፣ የሙስና ወንጀል ልዩ ባህሪና በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ላይ ስልጠና ሰጥተዋል ።

ዶ/ር አወቀ አያይዘውም እንደ ሀገር ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል ካልተቻለ በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከፋተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

የባለሥልጣኑ የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ክትትል ስራ አስፈፃሚ አቶ ሙሀመድ አማን በበኩላቸው፤ የስልጠናው ዋና ዓላማ ባለሙያዎች በዘርፉ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን እንዲከላከሉ ለማስቻል ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል ባለሙያዎች ባለስልጣኑ የአሰራር ስርዓቱን ከማዘመኑና ዲታላይዜሽን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ ስራዎች እንደቀነሱና በተለይም ሙስናንና ብልሹ አሰራርን አጥብቀው በመዋጋት የበኩላቸዉን ድርሻ እንደሚወጡ አሳስበዋል።

**ከገፅ 8 የዞረ**

አስፈላጊነቱን በተመለከተ ሠፊ ገለፃ አድርገዋል።በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእንስሳት ሪጉላቶሪ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ሀሚድ ጀማል በተሳታፊዎች የተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ላይ ሰፊ ምላሽ ሰጥተው በተለይም ሁሉም ባለሙያ ከሪፎርሙ ጋር ለመዋሀድ በክህሎትና በእውቀት እራስን ማብቃት ያስፈልጋል ብለዋል።

በባለስልጣኑ የእፅዋት ሪጉላቶሪ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ወንዳለ ሀብታሙ በበኩላቸው በመ/ቤቱ የሚሰጡ አገልግሎቶች በዲታላይዜሽን ሲስተም መሆኑን ገልፀው የሪጉላቶሪ የአሰራር ሲስተም የተሻለ እንዲበለፅግ ባለሙያዎች በአስተሳሰብ፣ በዕውቀትና በክህሎት እራሳቸውን እንዲያዳብሩ አሳስበዋል።

## የሪጉላቶሬ ስርዓቱ የተሳለጠና ውጤታማ እንዲሆን የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ትግበራ ወሳኝ መሆኑ ተገለፀ



የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የሪጉላቶሪ ስርዓቱ የተሳለጠና ውጤታማ እንዲሆን የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ትግበራ ላይ በአራቱም ክልሎች ለመጡ ሀላፊዎች ስልጠና ሰጥተዋል ።

በአገር አቀፍ ደረጃ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ትግበራ እተከናወነ ይገኛል ያሉት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ ሪፎርሙ የሪጉላቶሪ ስርዓቱን ለማሳለጥ ወሳኝ ሚና አለው ብለዋል።

አምባሳደር ጨምረውም ሪፎርሙ በተለይም ግልፅኝነትና ተጠያቂነትን እንዲሁም ብዝሀነትንና አካታችነትን ያረጋገጠ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎትን ይፈጥራል ብለዋል።

አክለውም ለአገራዊ የልማትና ግቦች ስኬት ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ነፃ፣ ገለልተኛና ብቁ የሰው ሀይል ለመገንባት ወሳኝነት አለው ሲሉ ተናግረዋል።

የእፅዋት ምርት ደህንነት ቁጥጥር ባለሙያና የሪፎርሙ የቴክኒክ ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ አንማው ይሄነው በበኩላቸው ባለስልጣኑ እስካሁን ያከናወናቸውን ተግባራትና የሪፎርሙ ዋና ዓላማ የአተገባበር ስርዓቱና

## ውፍረት ያስጨነቀው

——— ✦ ———

በምግብ ላይ ቀልድ የማያውቀውና ከዕድሜው በላይ እጅግ መወፈሩ ያስጨነቀው ወጣት ወደ ሐኪም ይሄዳል። ሐኪሙም በትህትና ተቀብሎት ስሙን፣ ዕድሜውንና ሌሎች የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን ከጠየቀው በኋላ፦

ሐኪም፦ እሺ! ሕመምህ ምንድነው?

ወጣቱ፦ ዶክተርዬ! እንደሚያዩኝ በጣም ወፍራም ነኝ። እናም ለዚህ መፍትሄ ለመፈለግ ነው የመጣሁት።

ሐኪም፦ (ጥቂት ካሰበ በኋላ) እሺ! ለጊዜው፤ ... ለአንድ ሳምንት ያህል ጠዋት አንድ፣ ቀን አንድ፣ እንዲሁም ማታ አንድ ዳቦ ብቻ እየበላህ ትቆይና፣ ከአንድ ሳምንት በኋላ ተመልሰህ ስትመጣ ለውጥህን እናያለን። ጨርሰናል!!

ወጣቱ በማመስገን በሩን ከፍቶ ከወጣ በኋላ ወዲያው ተመልሶ ይገባል።

ሐኪም፦ ምነው ተመለስክ የቀረ ነገር አለ?

ወጣቱ፦ ዶክተርዬ! አሁን ያዘዙልኝን የምወስደው ከምግብ በፊት ነው? ወይስ ከምግብ በኋላ?

.....







## የታላላቅ ሰዎች አባባል

- በዚች ምድር ሁሉም ነገር ያልፋልና ስታገኝም ከልክ በላይ አትደሰት፤ስታጣም አብዝተህ አትከፋ።(Socrates)
- ታላቁ ክብራችን አለመውደቃችን ሳይሆን፤በወደቅን ቁጥር መነሳታችን ነው። (Confucius)
- በተናደድክበት እያንዳንዷ ደቂቃ 60 ሴኮንድ የደስታ ጊዜ ታባክናለህ።(Ralph Waldo Emerson)
- እውቀት የነፍስ ምግብ ናት።(William Blake)
- ውድቀት ከተማርክበት ስኬት ነው።(Seneca)
- እያንዳንዷ የመከራ ህይወት ወደ ላቀ ደረጃ የምታሸጋግረን ድልድይ ናት።(Thackeray)




የሚከተልህ ሁሉ አድናቂህ አይደለም!!!

